# የሰማይ-ጠቀስ ፎቆች መልሶ ግንባታ

## የድረ-ገጽ ጥያቄ እና መልስ

20 ሴፕተምበር 2024

Amharic | አማርኛ

## የታወጀው ምንድን ነው?

የቪክቶሪያ መንግስት የሆምስ ቪክቶሪያ የትልቁ መኖሪያ ቤት ግንባታ (Big Housing Build) አካል ሆነው እንደገና የሚገነቡትን ቀጣይ በታዎች አስታውቋል። እነዚህ በታዎችም የሚከተሉት ናቸው፡-

- **139 Highett Street, Richmond,**
- **259 Malvern Road, South Yarra,**
- **6 & 8 Anderson Court Richmond,**
- **1 - 5, 7 & 9 Williams Court Richmond, and**
- **111, 119 & 127 Elizabeth Street Richmond**

## ይህ ማስታወቂያ ለተከራዮች እና ለአካባቢው ማህበረሰቦች ምን ማለት ነው?

በእነዚህ በታዎች ያሉ ተከራዮች የመልሶ ግንባታው ሂደት እንዲጀመር እና አዲስ ማህበራዊ መኖሪያ ቤቶች እንዲገነቡ፣ ስለ ወደ ሌላ በታ የመዛወሩ ሂደት ውይይት ይጀምራሉ።

ከበታ ወደ በታ የሚያዛውር ቡድናችን በእያንዳንዱ ቤተሰብ ፍላጎት እና ምርጫ መሰረት ተገቢውን መኖሪያ ቤት እንዲያገኙ ለማድረግ ከእያንዳንዱ ቤተሰብ ጋር ይሰራል። ይህም ምርጫቸው ሲሆን በአካባቢው ሰፈሮች ውስጥ ያሉ ቤቶችን ይጨምራል።

ይህ ሂደት ጊዜ ይወስዳል። በእነዚህ ማስታወቂያ በተነገረላቸው በታዎች የሚኖረው መዛወር በየካቲት 2026 ለማጠናቀቅ አላማ እናደርጋለን። መልሶ ግንባታው ከ 6 እስከ 8 ዓመታት ይወስዳል።

## የመዛወሩ ሂደት እንዴት ነው የሚሰራው?

ወደ ሌላ በታ ማዛወር ፈታኝ እንደሆነ ተረድተናል። ለዚያም ነው የኛ ቁርጠኛ የመዛወር ቡድናችን የግለሰቦችን ፍላጎቶች እና ምርጫዎች ለመረዳት እና ሂደቱን በተቻለ መጠን ከድጋፍ ጋር እና ቀላል ለማድረግ ከእያንዳንዳንዱ ከሚዛወር ቤተሰብ/ነዋሪ ጋር የሚገናኘው። ይህ የሚከተሉትን የመሳሰሉ አስፈላጊ ጉዳዮችን ያጠቃልላል፡-

- የተደራሽነት መስፈርቶች
- የጤና አገልግሎቶች እና አቅራቢዎች
- ትምህርት ቤቶች፣ መዋእለ ሕፃናት እና ትምህርት
- ማህበራዊ እና ማህበረሰብ ትስስሮች
- የመጓጓዣ አገናኞች እና ግንኙነቶች።

ተከራዮች ፍላጎታቸውን፣ ምርጫቸውን እና መስፈርቶቻቸውን የሚያሟሉ ሁለት ምቹ እና ተስማሚ መኖሪያ ቤቶችን እንደ ምርጫ ይቀርቡላቸዋል። ይህ ምርጫቸው ከሆነ በአካባቢያዊ ሰፈሮች ውስጥ ያለ የቤት አቅርቦትን ያካትታል።

ለተከራዮች አዲስ ቤት ስናቀርብ፣ ተስማሚ መሆኑን ለማረጋገጥ ንብረቱን የመመልከት እድሉ አላቸው። ተከራዮች የቀረበላቸውን ምርጫ ሲቀበሉ፣ የማዛወር ቡድናችን ከእያንዳንዱ ቤተሰብ ጋር ተስማሚ የሆነ ቤት የሚለቁት ቀን ያቀናጃል እንዲሁም በእንቅስቃሴው ላይ እገዛ ያደርጋል።

በመልሶ ግንባታው ወቅት ከዕቅድ ጀምሮ እስከ አዲሶቹ ቤቶች አቅርቦት ድረስ፣ የፕሮጀክት የተሻሻሉ መረጃዎችን በማቅረብ እና በአዲስ ቤቶች ንድፍ ወይም ዲዛይን ላይ አስተያየት ለመስጠት የሚያስችሉ እድሎችን በመፍጠር በቀጣይ እንገናኛለን።

## ሆምስ ቪክቶሪያ የመዛወር ወጪዎችን ይሸፍናል?

አዎ። ሆምስ ቤቶች ከቤትዎ እቃና ንብረት የሚያነሱ (removalists) ይመድባል ብሎም ሁሉንም የመንቀሳቀስ ወጪዎችን ይሸፍናል፡-

- ዕቃ ለሚያነሱት ሰዎች የሚደረጉ ክፍያዎች
- የማሸጊያ እቃዎች፣ ለምሳሌ ቴፕ፣ ካርቶኖች
- እንደ ኤሌክትሪክ፣ ጋዝ፣ ስልክ እና በይነመረብ ያሉ የመገልገያ ክፍያዎች መቀጠያ ክፍያዎች
- የደብዳቤ ማዞሪያ ወጪዎች
- ተከራዮች ወደ አዲስ ቤቶች በሚዛወሩበት ጊዜ የማይፈልጉትን ማንኛውንም ዕቃ ማስወገድ።

## ተከራዮች ቤት ለመቀየር ለመንቀሳቀስ እርዳታ ያገኛሉ?

ከቤት መቀየሪያ/መልቀቂያ ቀን በፊት ተከራዮች ማሸጊያ ካርቶኖች እና ቁሳቁሶች ይሰጣቸዋል እና እቃና ንብረት የሚያነሱ (removalists) የቤት እቃዎችን እና ሳጥኖችን አካላዊ እንቅስቃሴ ያካሂዳሉ።

ሆምስ ቪክቶሪያ ተከራዮች አብረዋቸው እንዲሄዱ የማይፈልጉትን እቃዎች እንዲወገዱ ያመቻቻል ይከፍላል ብሎም ተከራዮች ወደ አዲስ ሰፈር ከሄዱ ከአዳዲስ አገልግሎቶች ጋር እንዲገናኙ ያግዛል።

## ተከራዮች በአቅራቢያው መኖር ወይም እንደተጠናቀቀ ወደ አዲስ ቤቶች መመለስ ይችላሉ?

ተከራዮች ቀጣይነት ባለው ብቃታቸው፣ ፍላጎታቸው እና በአዲሶቹ ቤቶች ተስማሚነት ላይ በመመስረት የመልሶ ግንባታው ሲጠናቀቅ ወደ ነበሩበት አካባቢ የመመለስ መብት አላቸው።

ተከራዮች በወቅቱ በተሻለ ሁኔታ የሚስማማቸው ከሆነ በአዲሱ ቤታቸው ለመቆየት መምረጥ ይችላሉ።

## በዚህ ፕሮጀክት ውስጥ ተከራዮች እና ማህበረሰብ እንዴት ይሳተፋሉ?

በዚህ ፕሮጀክት በሙሉ የሰማይ ጠቀስ ህንጻዎች ተከራዮችን እና ማህበረሰቦችን እናዳምጣለን ብሎም ከነርሱ ጋር አብረን እንሰራለን።

ተከራዮች እና ማህበረሰቦች በአዳዲስ ቤቶች፣ ሰፈሮች እና ሌሎች ንድፎች ላይ ያላቸውን ሐሳብ የማሳወቅ እና አስተያየት የመስጠት እድሉ ይኖራቸዋል።

## ሆምስ ቪክቶሪያ ተከራዮችን ማዳመጡ ይቀጥላል?

አዎ። ተከራዮቻችን እና ማህበረሰቦቻችን በዚህ ፕሮጀክት ውስጥ ዋናው ተቀዳሚ ተግባራችን ናቸው እና እኛ እያዳመጥን ነበርን ደግሞም ከተከራዮች ጋር በመስራት ማህበረሰቦቻችንን: እሴቶቻችንን የተሰኘ - ሰማይ ጠቀስ ፎቆች መልሶ ግንባታው ሂደት ሁሉ ከተከራዮች ጋር እንዴት እንደምንገናኝ እና እንዴት እንደምንግባባ የሚመሩ የእሴቶች ስብስብ አዳብረናል።

የእኛ የመጀመሪያ እርምጃ ሁሉም ተከራዮች ጥሩ መረጃ እንዲኖራቸው እና ለእነሱ ያለውን ድጋፍ እንዲረዱ ማድረግ ነው።

ቁርጠኛ የቤቶች ቡድናችን ለእያንዳንዱ አካባቢ እቅዶችን ለመቅረጽ የተከራይ እና የማህበረሰብ ግብረመልስ ይሰበስባል። በየጊዜው አዳዲስ መረጃዎችን በመስጠት እና አስተዋፅኦ የሚያደርጉበትን እድሎችን በእያንዳንዱ የፕሮጀክቱ ደረጃ በመፍጠር ሁሉንም ሰው እናሳውቃለን።

## የድሮ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ለምን ጡረታ ማስወጣት አስፈለገ?

የድሮውን ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ጡረታ እንድናስወጣ የሚያደርጉን ብዙ ምክንያቶች አሉ። ፎቆቹ በሥራ ዘመናቸው መጨረሻ ላይ ናቸው፣ እና ከአሁን በኋላ ቪክቶሪያውያን የሚጠብቁትን አነስተኛ መመዘኛዎች አያሟሉም።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የሕንፃ ጉድለቶች እና ብልሽቶች (ኤሌክትሪክ፣ ቧንቧ፣ ሊፍት) በጣም የተለመዱ ሆነዋል እና እነዚህም በተከራዮች ላይ ተደጋጋሚ መስተጓጎል ያስከትላሉ።

የሕንፃዎቹ የቆየ ንድፍ/ዲዛይን ማለት ደግሞ ወደ ዘመናዊ ዲዛይን፣ ለኑሮ ምቹነት እና ተደራሽነት ደረጃዎች ማሻሻል ወይም ማዘመን አይቻልም ማለት ነው።

## ይህ ፕሮጀክት መቼ ይጀምራል እና መቼ ይጠናቀቃል?

ይህ ፕሮጀክት በ1950ዎቹ እና 70ዎቹ መካከል የተገነቡትን የሜልበርን 44 የቆዩ ሰማይ ጠቀስ የህዝብ መኖሪያ ቤቶችን በ2051 ቀስ በቀስ ጡረታ ያወጣል።

እያንዳንዱ መልሶ ግንባታ ለማጠናቀቅ ከስድስት እስከ ስምንት ዓመታት ይወስዳል።

ከ**ሳውዝ ያራ እና ከሪችመንድ ተከራዮች** ጋር ወደ ሌላ ቦታ የመዛወር እቅድ ለማውጣት የሚደረጉ ውይይቶች በቅርቡ በፌብሩዋሪ 2026 ይጠናቀቃሉ።

በ120 Racecourse Road እና በ12 Holland Court **ፍሌሚንግተን** እና 33 Alfred Street **ሰሜን ሜልበርን** ላይ በሚገኙት ተግባራዊ በሚደረግባቸው ጣቢያዎች የተከራዮች መዛወር በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ነው እና በሴፕቴምበር 2025 ለማጠናቀቅ እቅድ አለ።

## በተከራዮች መብት ላይ ለውጥ ይኖራል?

በተከራዮች መብቶች ወይም በይዞታ ዋስትና ላይ ምንም ለውጥ አይኖርም። ይህ በተዘወሩበት ቤት ለመቆየት ለሚመርጡ ተከራዮችን ይጨምራል።

ሁሉም የማህበራዊ ቤቶች ተከራዮች በ Residential Tenancies Act 1997 የተጠበቁ ናቸው።

## ተከራዮች እና ማህበረሰብ ተጨማሪ መረጃ የት ማግኘት ይችላሉ?

በዚህ ሂደት ግልጽ እና ወቅታዊ መረጃ እና ድጋፍ (የቋንቋ መረጃን ጨምሮ) ለማቅረብ ከተከራዮች እና ማህበረሰቦች ጋር በቅርበት እንሰራለን።

ምን እየተፈጠረ እንዳለ የበለጠ ለማወቅ እና ለፕሮጀክት ማሻሻያ እና የመረጃ ክፍለ ጊዜዎች ለመመዝገብ፣ **www.bighousingbuild.homes.vic.gov.au** ይጎብኙ፣ በተለያዩ ቋንቋዎች የተተረጎመ መረጃም እዚህ ያገኛሉ።

ተከራዮች ማንኛውም ጥያቄ ካላቸው፡-

- የአካባቢያቸውን የቤቶች ቢሮ ያነጋግሩ ወይም ከአካባቢያቸው የቤቶች ቢሮ ጋር ለመገናኘት ወደ **1800 716 866** (ከጠዋት 9 ሰዓት-ምሽት 5 ሰዓት፣ ከሰኞ እስከ አርብ) ይደውሉ ። አስፈላጊ ከሆነ አስተርጓሚዎች ይገኛሉ።
- ኢሜይል enquiries@homes.vic.gov.au
- በማህበረሰብ ጊዜያዊ የመረጃ ክፍለ ጊዜ ብቅ ብለው ይሳተፉ። ጊዜያት እና ቀኖች በድረ-ገጻችን **bighousingbuild.homes.vic.gov.au** እና በህንጻው አዳራሽ (ፎየር) ላይ ይለጠፋሉ።